# የፌዴራል ማንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን እንደገና
# <u>ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 260/2013</u>

የፌዴራል ማንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፣ መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የፌዴራል ማንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 260/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ማሻሻያ</u>

የፌዴራል ማንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ለማሻሻል የወጣው መመሪያ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው አባሪ ፪ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል፡፡

   "3(ሀ). የሀገር ወስጥ ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አሥር ዓመታት ወስጥ ሊሠራ ከታሰበው የግንባታ ሥራ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቢያንስ አንድ የግንባታ ሥራ በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማኅበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሠሩና ከሚወዳደሩበት ሥራ በዋጋ ቢያንስ 70% (ሰባ በመቶ) የሆነን ሥራ በአስተማማኝና በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡"

2. የመመሪያው አባሪ ፪ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሐ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሐ" ተተክቷል፡፡

   "3(ሐ). የግንባታ ሥራው ግምት ከብር አንድ ቢሊዮን እና ከዚያ በላይ ሲሆንና፣ ሥራ ተቋራጮች በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ሥራ ልምድ ዋጋ በአንድ ፕሮጀክት በሠሩት የሥራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁ ሁለት ወይም ሶስት ፕሮጀክቶች ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም የሁለቱ ወይም የሶስቱ ፕሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የሥራ ልምድ ዋጋ እንደቅደም ተከተላቸው ከግማሽ (1/2) ወይም ከሲሶ (1/3) በታች መሆን የለበትም፡፡"

3. የመመሪያው አባሪ ፪ ተራ ቁጥር 5 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 5 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል፡፡

   "5(ሀ) የሀገር ወስጥ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመታት ካስመዘገበው የግንባታ ሥራ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣ ሥራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሠራ የታሰበውን የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደሚቀጥለው ሙሉ ወር

Der/Hb/TA

በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈል እና ወጤቱን በ12 እና በ0.8 በማባዛት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ፕሮጀክት በሁለት ዓመት ከአንድ ወር ከ10 ቀን የሚጠናቀቅ በሆንና የዋጋ ግምቱ ብር 100 (አንድ መቶ) ሚሊዮን በሆን ሂሳቡ እንደሚከተለው ይሰላል፡፡"

$\frac{100,000,000}{26} x12x0.8=$ ብር 36,923,077

4. የመመሪያው አባሪ ፲ ተራ ቁጥር 12 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 12 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል፡፡

"12(ሀ). ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ወስጥ ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሠራ ከታሰበው የመንገድ ሥራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን የመንገድ ግንባታ ስራው የዋጋ ግምት ከብር 400 (አራት መቶ) ሚሊዮን በታች በሚሆንበት ጊዜ ሁለት ደረጃ ዝቅ ያለ እና ከዚያ በላይ የሆነ ፕሮጀክት ለተዛማጅ ስራ ልምድነት ሊያዝ ይችላል፡፡"

## 3 **ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን**

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ 4 **ቀን 2009 □ም**

ዶ/ር አብራሃም ተከስተ
**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር**